# የኢትዮጵያ ጠበቃ እንጂ የአንድ ብሔር አፈቀላጤ አይደለሁም

## ገላውዴዎስ አርአያ

7/30/2008

በጁላይ መጀምርያ ሰሞን ፡ የአመሪካን የነጻነት በዓል አጋጣሚን በመጠቀም የኢትዮጵያውያን የእግር ኳስ ፈደረሽን የስፖርት ዓመታዊ በዓሉን በዋሽንግቶን አድርጎት ስለነበር በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ካራቱ ማእዘናት ዩናይትድ ስተይትስ (ከካናዳና አውሮጳም ጭምር) በመጕረፍ በመናኸርያና የአመሪካን መናገሻ ከተማ በሆነችው ተገናኙ። የዚሁ የስፖርት ሥነ-በዓልም አጋጣሚ ተጠቅመው ልዩ ልዩ ፓርቲዎችና ስብስቦች መጠነኛ ስብሰባዎች በማካሄድ፡ የኢትዮጵያ ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታዎችን በማንሳት ተወያይተዋል። ከነዚሁም ፓርቲዎች አንዱ ኢሕአፓ/ዴሞክራስያዊ የፓርቲዎችና የምሁራን ሲምፖዝየም አዘጋጅቶ ስለነበረና ንግግር እንዳደርግም ጥሪ አድርጎልኝ ስለነበር ጥሪዉን በማክበር በጉባኤው ተሳትፍያለሁ። ከኔ ሌላ ጥሪ የተደረገላቸውና በሲምፖዝየሙ በመሳተፍ ንግግር ያደረጉ ደግሞ ዶ/ር ጌታቸው መታፈርያ፣ ዶ/ር ሙሉጌታ ስዩም፣ እና ዶ/ር ዳንኤል ክንዴ ይገኙበታል።

ሲምፖዝየሙ አልቆ ወደምናርፍባቸው ቦታዎች ከተመለስን በኋላ አንድ የድሮ ጓደኛየ ይደውልልኝና "ስላንተ በ ደብተራው ወብሳይት የተጻፈ አለና አይተኸው ካልሆነ ላመላክትህ ብየ ነው የደወልኩልህ" አለኝ። እኔም "አላየሁትም፣ ደብተራው ጋ ምናልባት አንዴ ገብቼ እንደሆነ እንጂ አይቼውም አላውቅም፣ ለማንኛውም ግን አየዋለሁኝ" አልኩት። ለበነገታው የአንድ ጓደኛየ ላፕቶፕ በመዋስ ደብተራውን ዳሰስኩት፣ በእርግጥም ስሜ ተጠቅሷል። ርእሰነገሩም <u>ከኃይለሥላሴ ጉግሳ እስከ ዶክተር ዜሮ፣ ከገላውዲዮስ አርአያ እስከ ስየ አብርሀ</u> ይላል። የደራሲው ስም አውግቸው ብሩ ነው፣ የብዕር ስም ለመሆኑ ጥርጥር የለውም። የጽሑፉ ይዘት ውጥንቅጥነትና መሰረተቢስነት ለማንም አዋቂና ተመክሮ ያለው ሰው ግልጽ ቢሆንም ቅሉ አንድአንድ ንጹህ፡ የዋህና ወጣት ኢትዮጵያውያን ግን ሊደናገሩ ስለሚችሉ በመጠኑም ቢሆን ገለጻ ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

በነገራችን ላይ ከፍ ብየ የጠቀስኳቸውን በሲምፖዝየሙ የተሳተፉ የምሁራን ስም ሳይጠቀስ የኔ ስም ብቻ በነቀፌታ አይሉት ዘለፋ መልክ ተጠቅሷል። እኔ ከማንም ገንቢ ነቀፌታ ነጻ አይደለሁም፣ እንድያውም ይኸንን ባህል በሕብረተሰባችን ውስጥ መልህቅ ይሰድ ዘንድ በተደጋጋሚ አግባብነት ያላቸው ጽሑፎች አቅርብያለሁ። በውሸትና አሉቧልታ የተመሰረተ ሂስ ወይም ተቃራኒ ክርክር ግን አልቀበለውም። አቶ አውግቸው ስለኔ የጻፉት ይኸውና፦

"ዶክተር ገላውዲዮስ አርአያ ኢሕአፓ ነበሩ ሲባል ብሰማም የዚያን ጊዜ ታሪካቸውን የማውቀው የለኝም። ለምን ድርጅቱን እንደተዉም በበኩሌ የማውቀው የለም። ዶክተር ገለውዲዮስን የማውቃቸው ወያኔ ከሆኑ ጀምሮ ነው። ወያኔን እያዳነቁና ኢሕአፓን እየተቹ የፃፉትንም መጽሀፍ አንብብያለሁ። ዶክተር ገላውዲዮስ የወያኔ

መፅሄት የነበረው ኮሜንቴተር አዘጋጅም ሆነው ወያኔን ፕሮፓጋንዳ ሲያሰራጩ የነበሩ ናቸው። ከዝያ እነ ገብሩ አስራትና ስዬ ከመለስ ሲጣሉ መለስ ዜናውን ተችተው ወደ ጎን ሆኑ። ወያኔታቸውን ሲተቹ ወይም ያለፈ አቅዋሜ ስህተት ነው ሲሉ ግን የሰማ ካለ ሊነግረን ይችላል። ዶክተር ዜሮና ዶክተር ገላውዲዮስ የተገናኙት በብተና ነው ወይስ በፀረ ኢሕአፓነት? ለዚህ መልሱ ብዙ ምርምር አይጠይቅም። ዶክተር ገለውዲዮስ በፀዳ የሕዝብ መድረክ ለመቅረብ በመጀመርያ ከወያኔታቸው ወይም ጠባብ ትግራዊ ስሜታቸው መላቀቃቸው መታወቅ አለበት። መለስ ዜናዊን መተቸት ወያኔን ማውገዝ አለመሆኑን ከስዬ አብርሃ ብቻ ሳይሆን ከነ አቶ አረጋዊም ሁኔታ የምናየው ነው"።

አቶ አውግቸው መጽሓፌን ያነበቡ አይመስለኝም፣ አንብበውት ከሆነም ወይ የመጽሓፉ ይዘት አልገባቸውም ወይም ደግሞ ሓቁን አኝከው ሳያላምጡ ተፍተውታል ማለት ነው እንጂ ወያኔን በማዳነቅና ኢሕአፓን በመተቸት ብቻ የጻፍኩት ነገር የለም። በእርግጥ በመጽሓፌ (Ethiopia: The Political Economy of Transition) አንዱ ራሱ የቻለ ምዕራፍ The Ethiopian Peoples Revolutionary Party (EPRP) and the Ethiopian Left በሚል ውስጥ Strengths and Weaknesses of the EPRP የሚል ንኡስ ርእስ አለ። አንባቢ ከንኡስ ርእሱ በቀላሉ መላምት ማግኘት ይችላል። የጻፍኩት ነገር ቢኖር የኢሕአፓን ጥንካሬና ድክመት፡ የፓርቲው አመሰራረትና የፖለቲካ ክንውኖች፡ ፓርቲው ከሌሎች ድርጅቶች (ህወሓት፡ ተሓኤ፡ ህግሓኤ፡ ኢዴሕ፡ ኦነግ ወዘተ) የነበረውን ግኑኝት ካልሆነ በስተቀረ ፓርቲውን በማጥላለትና ህወሓትን (ወያኔን) በመወደስ አልጻፍኩም።

ጸሓፊው የወያኔ የነበረውን ኮሜንቴተር የሚባል መጽሔት አዘጋጅና የወያኔ ፕሮፓጋንዳ አሰራጭ እንደነበርኩ አድርገው ያስቀመጡት ዓይን ያወጣ ውሸት ነው። ድሮ በመልካም የኢትዮጵያ ባህል መሠረት አንድ ግለሰብ ዕድሜው ከሃምሳ በላይ ከሆነ ግብረገባዊ ጸባዮችና ሃቅነት ይጠበቅበት ነበር። አሁን ግን በውሸት የተካኑ ግለሰቦች በብዕር ስም ሽፋን እውነትን ሲዳሽቁ ማየቱ እጅግ በጣም የሚያሳዝን ጉዳይ ነው። የሆኖ ሆኖ ግን ኮሜንቴተር የወያኔ መጽሔት አልነበረም፣ አዘጋጁና አታሚው በሚሺጋን የሚኖር ግለሰብ ነበር። ለነገሩ በዚሁ መጽሔት ያቀረብኳቸው ታሪክና ሂስ-አዘል ድርሰቶች ሦስት ሆነው የመጀምርያው ስለ ትግራዎት በኢትዮጵያ ፖለቲካ የተጫወቱት ሚና፣ ሁለተኛው ስለ ሕገ መንግሥታዊና ፌደራላዊ አወቃቀር በኢትዮጵያ፣ ሦስተኛው ደግሞ ስለ ዴሞክራስያ ታሪካዊ አመጣጥና የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የሚገልጹና የሚተነትኑ ናቸው።

አቶ አውግቸው "ዶክተር ዜሮና ዶክተር ገለውዲዮስ የተገናኙት በብተና ነው ወይስ በጸረ ኢሕአፓነት?" በማለት የሰነዘሩት ባንዳፍታ ጉጉት የሚያስይዝና ለመሳለቅያ የተጋለጠም ሓተታ ይመስለኛል። መጀመርያ የፈለገውን ጥላቻና ንዴት ቢኖርም፡ ሕብረተሰባችን በሚፈቅደው መልካም ባህልና ሥነስርዓት የአንድ ግለሰብ ስም እንደ ደንቡ መጥቀሱ አስፈላጊ ይመስለኛል። ዶክተር ዜሮ ብሎ ማለት ግን ራስን ማዋረድና አዘቅት ውስጥ መክተት ነው የሚሆነው። ተራ የጅራፌ አነጋገርና የውዳቂ አስተሳሰብ ነጸብራቅም ሆኖ አግኝቼዋለሁ። እኝህ ዶክተር ዜሮ የተባሉት ዶ/ር ጌታቸው በጋሻው ለመሆናቸው አንድም ሁለትም የለውም፣ እኔ እስከማውቃቸው ድረስ ደግሞ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄና በኢሕአፓ ገንቢና አወንታዊ

አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን ነው። ትውውቃችን ደግሞ አሁን ሳይሆን የዛሬ 36 ዓመት በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ (አሁን አዲስ አበባ ዩኑቨርሲቲ) ነው። አሁን እንደገና የተገናኘነው በሲምፖዝየሙ እንጂ ኢሕአፓን ለመበተን ሴራ ለመጠንሰስ አይደለም። አቶ አውግቸው ማወቅ ያለባቸው ነገር ቢኖር ግን ኢሕአፓ'ኮ የተበተነው አሁን አይደለም፣ ድርጅቱ መበታተን የጀመረው በፈረንጅ አቆጣጠር በ1970 መጨረሻዎቹና በ1980 መጀመርያዎቹ ነው። እስከዛው ግዜ ድረስ ኢሕአፓ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ከፍተኛ ሚና መጫወት ብቻ ሳይሆን የባላይነትም ነበረው፣ በዛን ግዜ ኢሕአፓ ለደርግ አስፈሪ ቅዠት አሳድሮበት ነበር፣ ሌሎች ተቀናቃኝ ድርጅቶችን አስበርግጎ ነበር፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ እጅግ ተወዳጅነት አግኝቶ ስለነበር በዓለም ደረጃም ዝናው ተወዳዳሪ አልነበረውም። የሆኖ ሆኖ ግን የኢሕአፓ አመራር ከፍተኛ ስሕተቶችን ፈጽሟል፣ ከስሕተቶቹም አንዱ የአመራር አባላትና ካድሬዎች በዋና ዋና ከተሞች ብቻ በማሰለፍና ለደርግ ጥቃት ማጋለጡ እንዲሁም ሠራዊቱን (ኢሕአሰ) የሁለተኛ ደረጃ ሚና እንዲጫወት ማድረጉ ነው። ሓቁን ለመናገር ግን ኢሕአፓ የተበተነው በገዛ ድክመቱና የአመራር ጉድለት ብቻ ሳይሆን በውጭና በውስጥ ጠላቶችም ጭምር ነው፣ ፓርቲው በልዩ ልዩ ተቀናቃኝ ድርጅቶችና በደርግ ኃይሎች ወጥመድ ውስጥ ከመግባቱም በላይ ስብስቦችና ግለሰቦችም ሰርገው በመግባት የድርጅቱን ኃይለ-መዋቅር እንዲዳከምና ብሎም እንዲፈራርስ አድርገዋል።

ወደ አዲሰ አበባ ዩኒቨርሲቲ ልመለስና፣ ኢሕአፓና ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች በይፋ መንቀሳቀስ ከመጀመራቸው በፊት፣ ታሪክ የራሱ ሂደትና ሕግጋት ስላሉት፡ በተማሪ ንቅናቄ በመጠኑም፡ በክፍተኛ ደረጃም የተሳተፍነው እንደየፈርጁ የታሪክ ዕጣ ስለደረሰብን በተለያየ አቅጣጫዎች ተጉዘናል።

አንዳንድ ጓዶች ግን እኛ የተጓዝነውን ጉዞ ማድረግ አልቻሉም፣ ከየካቲት የኢትዮጵያ አብዮት ፍንዳታ በኋላ እምብዛም ሳይቆዩ የቀይ ሽብር ሰለባ ሆነው ተቀጨ። መጽሓፌም ለነዚህ ከኢትዮጵያ አብራክ የወጡ ጀግኖች መታሰቢያ ትሆን ዘንድ አበርክችያታለሁ። ሌሎቹ ኢሕአፓን መስርተው ታግለዋል፣ በአንጻሩ መኤሶን ሆነው ከደርግ ጋር እጅና ጓንቲ ሆነው የሰሩም አሉ፣ አንዳንዶቹም ከኤርትራና ከኦሮሞ ነጻ አውጪ ድርጅቶች ተቀላቀሉ፣ ሌሎቹ ደግሞ በህወሓት ዙርያ ተደራጅተው ሲታገሉ ከቆዩ በኋላ ደርግን በማቸነፍ የመንግስት ስልጣንን ይዘዋል። አንድ ምሁር ኢትዮጵያዊ ይኸንን የተመሰቃቀለ፡ ውስብስና የታሪክን አስደንጋጭ ሚስጢርነትን አስመልክቶ ሲያትት "የጠበቅናቸውን ሳይሆን ያልጠበቅናቸውን ናቸው በትረ ሥልጣኑን የጨበጡት" አለ ይባላል።

አሁንም ቢሆን የታሪክ አስደንጋጭ ሚስጢርነት መከሰቱ ስለማይቀር፡ የኢትዮጵያችንም የወደፊት ዕጣ ምን እንደሚመስል በቅጡ ማወቅ ስለማንችል፡ ብያንስ ብያንስ ከጅራፌ ፖለቲካ ወጥተን ላገራችን የሚበጅ ትላልቅና ገንቢ አጀንዳዎች ብንይዝ ነው አስተማማኝ የለውጥ ስትራተጂዎችን መቀየስ የምንችለው። ለዚህም ነው ኢትዮጵያን በተመለከተ ዓበይት ጥያቄዎችን በማንሳት አያሌ ጽሑፎችና መጻሕፍት ያቀረብኩት። የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠበቃ እንጂ የትግራይ ብቻ አፈቀላጤ እንዳልሆንኩም አንባቢ በነዚህ ጽሑፎቼ ማወቅና መረዳት ይችላል። ሓቁን ለሚሻ ሁሉ የጻፍኳቸውን ድርሰቶችና አቃቂሮች በልዩ ልዩ የኢትዮጵያውያን

ድረገጾች፣ ራሴ በፈጠርኩት www.africanidea.org እና ጉጉል (google) በማድረግም ማግኘት ይቻላል። የአብዛኞች ጽሑፎቼ ርእሰነገሮች አፍሪቃና ኢትዮጵያን ያካተቱ ሆነው አልፎ አልፎ ግን ስለ ትግራይና ስለ ሌሎች የኢትዮጵያ ብሔሮችም ጽፍያለሁ። በ2003 ዓ.ም. ለምሰሌ Hail the People of Tigray, Defenders of Ethiopian Sovereignty and Custodians of its Civilization በሚል ርእስ ጽፍያለሁ። ሚሸላ ሮንግ የተባለችው እንግሊዛዊት ጋዜጠኛ ለጻፈችውም ዘለፋ አጸፌታውን በመመለስና የትግራይን ሕዝብ ምንነት በማስከበር ጽፍያለሁ። ይህ የምኮራበት እንጂ የማፍርበት ጉዳይ አይደለም። በአፄዎቹ ዘመነ መንግስታት የኦሮሞ ብሔር የደረሰበት በደልና ግፍ በመጽሓፌና ሌሎች ጽሑፎቼ ከሳመርኩበት በኋላ የብሔሩ አባላት ግን እኩልነትና ፍትሕ በነገሰባት ኢትዮጵያ በሰላም አብረው እንዲኖሩም ሓሳብ አቅርብያለሁ። በተመሳሳይ ሰለ አማራ ብሔር የጻፍኩትን በከፊሉ ይኸውና፦

“ከፖለቲካው ስርዓት ባሻገር አንድን ብሔር በደፈናው ያለማውገዝ። ከዚህ ቀደም በሌላ ጽሑፌ እንዳቀረብኩት ሁሉ ማንኛውም ሰው ገና ለገና የዚሁ ብሔር አባል ልሁን ብሎ አይወለድም፣ እንዲህ ያለ ክስተት ታይቶም ተሰምቶም አያውቅም፣ ለወደፊትም አይኖርም። ስለሆነም አንዳንዶቻችን የትግራይ ተወላጆች ነን፣ አንዳንዶቻችን ደግሞ አማራ፡ ኦሮሞ፡ አኘዋክ፡ አፋር ወዘተ ነን። ሌሎቻችን ደግሞ ወይ የሁለት ወይም ደግሞ የሶስት ብሔር ቅይጥ ልንሆን እንችላለን። ባሁኑ ግዜ ደግሞ ቅይጥነት ማለፍያ ነው የሚያሰኝ ሳይሆን አይቀርም፣ ምክንያቱም ለአንድነታችን አመቺ ሁኔታ ይፈጥርልናል። የሆኖ ሆኖ ግን ይኸንን ነጥብ ያነሳሁበት ምክንያት አንድን ብሔር ወይም የአንድን ብሔር ሰዎች በደፈና ከማውገዝ ይልቅ ያለውን የፖለቲካ መዋቅርና የመደብ አሰላለፍ በጥልቀት መመርመር አስፈላጊ እንደሆነ ለማስታወስ ያህል ነው። ለምሳሌ በአፄ ኃይለስላሴ ግዜ የአማራ ብሔር የሚወገዘበት ግዜ ነበር፣ በተሳሳተ መንገድም አማሮች በሙሉ የመደብ ተጠቃሚዎች እንደነበሩ ይቀርብ ነበር። በእርግጥ ተጠቃሚዎችና ነፍጠኞች ነበሩ፣ ግን በድህነትና በቸነፈር የሚሰቃዩ፣ የዕለት ዳቦ የማያገኙ፣ ደህናም ከተባለ በደሳሳ ጎጆ የሚኖሩ አማሮች እንደነበሩና እንዳሉ የምናውቀው ሓቅ ነው። ከፍ ብየ እንደጠቀስኩትም የዚሁ ብሔር ተወላጆች ሆን ብለው ማንነታቸውን የለጠፉ ሳይሆን እንዳጋጣሚ የሆነ ነገር ነው። በተጨማሪ የዚሁ ብሔር ተወላጆች፡ እንደ ሌሎች ኢትዮጵያውያን፡ ለኢትዮጵያ አንድነትና ነጻነት ታግሏል።” ይህ ጽሑፍ በ2006 ዓ.ም. <u>ገድለ-ጻድቃናት ዘኢትዮጵያ ኣክትሚል ወይ?</u> በሚል ርእስ በጻፍኩት ውስጥ ይገኛል፣ ወብሳይቱን ማለትም www.africanidea.org በመጎብኘትም ጽሑፉን ማየት ይቻላል። ስለ አማራ ብሔር ገለጻ ማድረግ የፈለግኩት በኢትዮጵውያን ዘንድ የተወናበደ አመለካከት ስለነበረ እንጂ የአማራ ብሔር አፈቀላጤ ለመሆን አልነበረም፣ ፖለቲካ ዓለም ውስጥ ከገባሁ ጀምሮ የኢትዮጵያ ጠበቃ ሆኜ ብቻ ነው የተንቀሳቀስኩት።

በሲምፖዝዮሙ ለመንደርደርያ ያቀረብኩት የመወያያ ርእሰነገር <u>የጎሳ ፖለቲካና የኢትዮጵያ አንድነት</u> የሚል ሆኖ ትኩረቱ ግን በተሳሳተ የመንግስት የቋንቋ ክልሎች ፖሊሲ ብቻ ሳይሆን በውጭ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን የጎሳ አደረጃጀትም ጭምር ነው። ደግሜ ደጋግሜ እንዳስቀመጥኩት ሁሉ ባሁኑ ግዜ ኢትዮጵያ-አቀፍ (የልዩ ልዩ ብሔሮች አባላት ያሉበት) ድርጅት አለ ማለቱ አዳጋች ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ከፍ ብየ እንደጠቀስኩት ኢሕአፓ በኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ

ድጋፍ አግኝቶ የነበረው የእውነት ኅብረ-ብሔር ፓርቲ ስለነበረና ከሞላ ጐደል ብሔሮቹን በጠቅላላ አቅፎ ስለነበር ነው። የድርጅቱ አባላት አማራ፡ ትግራይ፡ ኦሮሞ ብቻ ሳይሆኑ ጉራጌ፡ሲዳማ፡ ሃድያ፡ ካምባታ፡ ዶርዜ/ሃይዞ፡ አደሬ፡ ሱማሌ፡ አፋር፡ አገው፡ ሳሆ፡ ሺናሻ ሳይቀሩም ነበሩበት፣ ከዛም አልፎ ተርፎ ኤርትራውያን (ቢን ዓሚሮች ሳይቀሩ) የኢሕአፓ አባላት ሆነው ተሰልፈው ነበር። ስለሆነም ምልአተ ኢትዮጵያን ያስተናገደ ድርጅት እስካልተፈጠረ ድረስ የኢትዮጵያ ትንሳኤ እውን ሊሆን አይችልም። ምናልባት ለወደፊቱ ወይ ኢሕአፓ/ዴሞክራስያዊ ወይ ደግሞ ልዩ ልዩ የብሔር ድርጅቶች ለኢትዮጵያ ድህንነትና ትንሳኤ ብለው ሃገራዊ ቅንጅት ከፈጠሩ የኢትዮጵያ ብሩህ ዕድል የሚከሰት ይመስለኛል። አሁን በቅርቡ በአራት ድርጅቶች (United Ethiopian Democratic Force-UEDF-, Oromo Federalist Democratic Movement-OFDM-, Somali Democratic Alliance Forces-SDAF-, Arena Tigray for Democracy and Sovereignty-ATDS-) አነሳሽነት መልካም እንቅስቀሴ ተጀምረዋል። ግን ገና አልተፈተኑም። የነዚህ ድርጅቶች መፈተን ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሃውና የዓለም አቀፍ ዝምድናዎችና ግንኙነቶችንም በቅጡ መገንዘብና ማጤን ያለብን ጉዳይ ነው።

በውጭ የሚገኙ ኢትየጵያውያን ግን ለኢትዮጵያ የሚበጅ ስተራተጂ መቀየስ አልቻሉም፣ የአንድነት ጎዳና አልዘረጉም፣ ከባዶ 'እናት አገር ኢትዮጵያ' መፈክር ባሻገር የእውነት ኅብረት መመስረት አልቻሉም። በአንጻሩ በልዩነቶቻቸውንና በጎጥ አወቃቀራቸው ላይ ነው ያተኮሩት። ይህ እጅግ በጣም አደገኛ የፖለቲካ አዝማምያ ነው። በሽታም ሳይሆን አይቀርም የሚል እምነት አለኝ። በሽታው በብዙ መንገድ ነው የሚንጸባረቀው፣ በጽሑፍ፡ በሬድዮ፡ በኢንትርነት የሚሰራጩ ዜናና ትችቶች አንድነትን የሚበጣጥሱ እንጂ የሚያጐለምሱና የሚያዳብሩ አይደሉም። ከነዚሁም ከልክ ያለፉ፡ ቅጥ ያጡ የኢንተርነት ጀግና ስብስቦች አሉ። ዋና ተግባራቸውም የግለሰቦች ስም ማጥፋትና መርገም፣ ከዛም ለጥቆ በአንድ ብሔር ላይ ዘመቻ ማካሄድ ነው። ምሳሌዎች ላቅርብላችሁ፡-

ለስምፖዝዮሙና እግር ኳስ ጨዋታ ዋሺንግቶን ዲሲ በቆየሁበት ግዜ አዲሱ የአማርኛ መጽሓፌን (መንከባከብና ማስወገድ ያለብን ባህሎች) ከአታሚው ለመሰብሰብ ሄድኩና አጋጣሚ ሆኖ በሌሎች ኢትዮጵያውያን የተደረሱ መጻሕፍትም አየሁኝ። ከነዚህ አንዱ መጽሓፍ <u>ሥልጣን ተሻሚ ትግሬዎችና የኢትዮጵያ አንድነት</u> የሚል ርእስ ያዘለ ነበር። ለምልክት/መግለጫ የተቀመጠ መጽሓፍ ስለነበረም ልገዛው አልቻልኩም፣ ግን በነበረኝ አጭር ግዜ ገለጥ ገለጥ አድርጌ አየሁት። ደራሲው የትግራይ ተወላጆች የሆኑትና በተለያየ ግዜ ስልጣን የጨበጡ ሁሉ ማለትም ከጥንት ጀምሮ እስከ ደጃዝማች ገላውዴዎስ (የሽሬ ገዢ በ16ኛው ክፍለ ዘመን)፣ ከአፄ ዮሃንስ እስከ የአሁኑ ወያኔና ፓትርያርክ አቡነ ጳውሎስ ባንድ ገበታ በማስቀመጥ ይረግማቸዋል። እውነቱን ለመናገር አፄ የሃንስን በተመለከተ ደራሲው ንጉሰ ነገስቱ የሰሩትን በጎ አድራጎትና ላደረጉት መስዋእትነትን ይጠቅሳል። መልእከቱ ግን የትግራይን ሕዝብ ከመዝለፍ ነጻ ልያደርገው አልቻለም። የትግራይን ሕዝብ እየሰደቡ የኢትዮጵያ አንድነት እንጠብቃለን ማለት ደግሞ ዘበት ነው።

ከዋሽንግቶን መልስ በኋላ አንድ ሌላ ጓደኛየ 'ብቅ ጥልቅ ብሎ የጠፋ ያላየኸው ጽሑፍ አለና እልክልሃለሁ' ብሎ ካስታወቀኝ በኋላ የኮምፒተር እትሙን ላከልኝ።

ርእሱ <u>የዕውነት ስርየቱ የታሪክ ትምህርቱ</u> የሚል ሆኖ ደራሲው ደግሞ ነብለት ኀብስቱ ነው። ጽሑፉን ሳነበው ከሞላ ጐደል የቃላት አወዳደቅና የአማርኛው ዘይቤ፡ አንጻራዊ በሆነ መንገድ ስገነዘበው የአቶ ነብለትና የአቶ አውግቸው ጽሑፎች አንድ ናቸው ማለት ይቻላል። ጸሃፊዎቹም 'አንድም ሁለትም' ሊሆኑ ይችላሉ፣ በአንድነትና ላንድ ዓላማ እንደሚሰሩ ግን ጥርጥር የለውም። የአቶ ነብለት ትችት በአቶ አረጋዊ በርሀ ያተኰረ ሆኖ የትግራይን ሕዝብ የሚዘልፍና ዝቅተኛ አመለካከትን የሚያንጸባርቅ ጽሑፍ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ጸሓፊው በ1993 የወያኔ ወታደሮች ወልቃይት ከሚገኘው አንድ መንደር (የመንደሩ ስም አልተጠቀሰም) ከገቡ በኋላ እዛው የነበሩትን ወንዶች በሙሉ ይገድሏቸዋል፣ ሚስቶቻቸውንም ይደፍሯቸውና ዲቃላዎች እንዲወልዱ ያደርጓቸዋል ይላል። በጣም የሚገርም ነው! ይህ አስጸያፊ ድርጊት ተደርጎ ከሆነ ወታደሮቹ በሕግ ፊት ቀርበው መቀጣት አለባቸው፣ መንግስቱም በሓላፊነት መጠየቅ አለበት። አሉቧልታ ከሆነ ደግሞ ጸሓፊው የኋላ ኋላ በሓላፊነትና በሕግ ይጠየቃል።

ጸሓፊው ወልቃይትን አስመልክቶ ያላወቀው ታሪካዊ እውነታ እንዳለም ካጻጻፉ ልረዳ በቅችያለሁ፣ እንዲህም ይላል፦ "ዛሬ የወልቃይት ሴቶች ማስወረድ ስለማይፈቀድላቸው የጠላቶቻቸውን ዲቃላዎች ተገድደው በማሳደግ ላይ ይገኛሉ። እነዚህ ዲቃላዎችም ናቸው ነገ እነ አረጋዊ በርሄ ላቀዱት ሬፈረንደም (ውሳኔ-ሕዝብ) ተስፋ የተጣለባቸው። ልጅ ከአባቱ ይጠራል ነውና በነዚህ ዲቃላዎች ድምፅ ነው የወልቃይትና ለሙ የጎንደር መሬት ቋሚ የትግራይ መሬት እንዲሆን የታቀደው።" አቤት አቤት! ይህ አባባል መቾም ያድህነነ፡ ይሰውረነ ከመዓቱ! የሚያሰኝ ነው። አገራችንም በእንዲህ ያለ ጭራቅ አስተሳሰብ ያላቸው ስብስቦች እንዳትወድቅ የሁላችን ታሪካዊ ሓላፊነት መሆን አለበት። እግረ መንገዴ ግን የወልቃይትን ጉዳይ በሚመለከት ያለኝን አስተያየት ላንባቢ ማቅረብ እፈልጋለሁ። ጸለምቲ እና ወልቃይት ትግርኛ ተናጋሪ ስለሆኑ ብቻ ከትግራይ ክልላዊ መስተዳድር ማስቀመጡ ትክክል ላይሆን ይችላል። በመሰረቱም የቋንቋ ክልልች ከመርህም ከፖሊሲም አንጻር ስሕተት ነው የሚል እምነት ነው ያለኝ። ነገር ግን የኢትዮጵያን ታሪክ በደምብ ከመረመርነው ጸለምቲ ና ወልቃይት ለብዙ ዘመናት ከትግራይ ጋር ነው የተስተዳደሩት። ከዘመነ መሳፍንት 45 ዓመት በፊት ወይም ከአፄ ፋሲል ስምንት ዓመት በፊት ማለትም በ1624 እአአ አንድ ማንወል ባራዳስ የተባለ የፖርቱጌዝ ሚስዮናዊ ስለ ትግራይ የጻፈው መጽሓፍ አለ። ትግራይ ምንጊዜም የኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍለሃገርና የስልጣኔዋ መናኸርያ ነው የነበረው፣ ስፋቱ ግን ካሁኑ ትግራይ አራት እጥፍ ነበር። በባራዳስ መጽሓፍ ውስጥ ያለውን የትግራይ ካርታ እንደሚያሳየው ከሆነ ክፍለሃገሩ በስተሰሜን ያሁኑ ጠቅላላ ኤርትራ ከነደሴቶቹ (ዳህላክ) ያካተተ ሲሆን፣ በደቡብ ከአልውሃ ይጀምርና በሰተምዕራብ የተከዜን ወንዝ ተከትሎ ወደ ውስጥ ገባ ብሎ እስከ ሊማሊሞ፣ ከዛም የቆላውን መሬት ይዞ እስከ ምዕራባዊ ቆላ (አሁን ተሰነይ/ኤርትራ) ሲያጠቃልል በምስራቅ በኩል ደግሞ የቀይ ባሕር ዳርቻ ተከትሎ በዘመናችን ምስራቅ ወሎ፡ ምስራቅ ትግራይ (የአሁኑ ኤርትራም ጭምር) ያካተተ ነበር። የባራዳስ ካርታ ማየት ከፈለጉ www.africanidea.org ይጎብኙ።

በዘመነ መሳፍንት ግዜ በተለይም በራስ ሚካኤል ስሑል ዘመን ሰሜን ኢትዮጵያ ከጎንድር ሆኖው ያስተዳዱሩት ስለነበረ ወልቃይትና ጸለምቲ እንደ መሃል አገር

ነበር የሚታየው፣ በደጃዝማች ስባጋድስ ግዜም በተመሳሳይ መልክ የትግራይ አካል ሆኖ ቢተዳደርም የስሜኑ ደጃች ማርየ የደጃች ስባጋድስ ተቀናቃኝ ስለነበሩ ግዛታቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ከደጃች ስባጋድስ ጋር ባደረጉት ጦርነት ሁለቱ መሳፍንት በ1831 ዓ.ም. ስለሞቱ ለደጃች ውቤ አመቺ ሁኔታ ፈጠሩላቸው። እዚህ ላይ ዝርዝር ሳልገባ ከደጃች ውቤ በኋላ አፄ ቴዎድሮስ ከዛም አፄ ዮሃንስ ተከትለውም አፄ ምንሊክ በቅደም ተከተል ሲነግሱ ትግራይ እንደ ማንኛውም ክፍለ-ሃገር ወይም አገር አንዳንዴ ሰፍቷል፡ አንዳንዴ ደግሞ ጠበዋል። ራስ ተፈሪ መኰንን አፄ ኃይለሥላሴ ተብለው ከነገሱ በኋላ ልክ በነገሱበት ግዜ የራስ ጉግሳና የራያ ዓዘቦ ዓመጽ በትግራይ ተነሳስቶ ስለነበር አፄው በራስ ጉግሳ ላይ ዘመቻ አካሂደው አቸነፏቸው። ራስ ጉግሳ ከተቸነፉ በኋላ ያስገብሩትና ያስተዳዱሩት የነበረ ወልቃይትና ጸለምቲ በአፄ ኃይለሥላሴ ትእዛዝ በ1930 ዓ.ም. ከጎንደር እንዲስተዳደር፣ ቀጥሎም በ1957 ዓ.ም. ቤገምድርና ስሜን ተብሎ እንዲስተዳደር ተደርጓል።

ስለዚህ አቶ ነብለት አልተገነዘቡትም እንጂ እንኳንስ ትግራይና ጎንደር በኩታ-ገጠም መልክአ-ምድር የሚኖር አንድ ዘርና አንድ ሕዝብ፡ ጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ (ኤርትራም ጭምር) በታሪክ፡ ባባህል፡ በቋንቋ፡ በኃይማኖት የተቆራኘ ሆኖ በመልክ ተመሳሳይነትም አንዱ ካንዱ በጣም ስለሚመሳሰል፣ ልሳኑ ካልከፈተ በስተቀረ ለይቶ ለማወቅ እጅግ በጣም አዳጋች ነው የሚሆነው። ይህ ታሪክ የለገሰልንን ጠንካራ ጎናችን ስለሆነ እንደ እንቍላል ወድቆ እንዳይሰበርብን በከፍተኛ ጥንቃቄና እንክብካቤ መያዝ ይኖርብናል።

እነ አቶ ነብለት ግን ጠንካራ ጎናችንን ትተው በደካማ ጎናችን ላይ ያተኮሩ ይመስላሉ። የመደብ ቅራኔና አሰላለፍ ከናካቴው በመርሳትም በአንድ ብሔር ላይ ስለተረባረቡ የትግራይ ሕዝብ የሚጠላበት መንገድ እየቀየሱና የኢትዮጵያ አንድነት ደግሞ በመሸርሸር ላይ ይገኛሉ። የዚህም ዓይነተኛ ምሳሌ የአቶ ነብለት ኢርትዓዊና መሰረት የሌለው ግንዛቤ በሚከተለው ዓረፍተ ነገር ይንጸባረቃል። አቶ ነብለት እንዲህ ይላሉ፦ "የትግራይ ተወላጆች የተመቻቸላቸውን ሁኔታ ተጠቅመው በማንኛውም የአገሪቱ ግዛቶች እንደ ልባቸው ተዘዋውረው የመሥራት ነጻነት አላቸው። ሥራ ደግሞ ዳቦም ሃብትም ነው። ሃብትም ከበሬታን ያጎናፅፋል። ሁሉም ባለው ያምራል እንዲሉ ያለው ጠግቦ ማደር ብቻ ሳይሆን የስልጣንም ባለቤት ነው። ለትግራይ ሕዝብ ይህ ሁሉ አልተጓደለበትም።"

ጸሓፊው በእርግጥ በጠራራ ፀሓይ የጨለመባቸው ይመስላል፣ የትግራይ ሕዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተለየ መብት ወይም ትርፍ ጥቅም አላገኘም። በእርግጥ በመቀሌና ዙርያው ብዙ ለውጥ አለ ማለት ይቻላል፣ ይህ ክስተት ግን በባህርዳር፡ በአዋሳ፡ በናዝሬት፡ በሃረርና በሌሎች ክልሎችም የሚታይ ነው። ድሮ አበው ሲተርቱ (በትግርኛ) "አይበልዐ አይሰተየ፡ ጎንደር ከይዱ ሞተ" ይሉ ነበር። የትግርኛው አባባል በቀጥታ ወደ አማርኛ ሲተረጐም (ቤቱ አይመታም እንጂ) "አልበላ አልጠጣ፡ ጎንደር ሄዶ ሞተ" ማለት ነው። ሰፊው ትርጓሜው ግን 'ወድያና ወዲህ ሲንገላታ፣ ሲግርና ሲጥር አሳለፈው እንጂ አላለፈለትም፡ ከመሃሉም ሞት ደረሰበት' ነው። የትግራይም ሕዝብ አሁንም ቢሆን እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ላቡን እያንጠፉጠፈ የዕለት ተዕለት እንጀራውን እያሳደደ ነው ያለው።

ከሁሉ በጣም ያሳዘነኝ ግን አቶ ነብለት ኀብስቱ ጀግናው ዘርኡ ክሕሽን አስመልክቶ የሰነዘሩት ሓተታ ነው። እንዲህም ይላሉ፦ "ኢሕአፓ…ከወያኔ ጋር ለመስራት ተደጋጋሚ ውይይቶችን አካሂዶ ነበር። ዘጠኝ ግዜ በተደረጉት ዘጠኙንም ውይይቶች ወያኔን ወክሎ ያከሸፋው አረጋዊ በርሂ ነበር…ቀደም ሲል የኢሕአፓ አባላት ይህ እንደሚመጣ ገምተው ስለነበር ይህች ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም ተሃትን በለጋዋ እንምታት ሲሉ ዳሩ ከውሃ ደም ይወፍራል የሆነባቸው እነ ዘሩ ኩህሽን [ዘርኡ ክሕሽን] "ይህማ እውነትም ጠባቦች እንደሚሉት ትምክህተኝነት ነው። ስለ ብሄሮች እኩልነት እየሰበክን የቢሄር ጥያቄን አንስቶ የሚታገልን ድርጅት ማጥፋት ሂፖክራትነት ነው" በማለት በኢህአሠ ሞራል ላይ ቀዝቃዛ ውሃ ቸለሱ። እነዚህ የውስጥ አርበኞች ብዙዎቻችን ባልገባን መንገድ የሠራዊቱን ወኔ ሰልበውና ፍላጎቱን አብርደው ለነ አረጋዊ በርሄ ድንገተኛ አደጋ አመቻቹት።"

በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገ፣ ኢሕአፓን ከመሰረቱት ቀደምት መሪና ዕድሜ ልኩን ለሃገሩ ለኢትዮጵያ ዓብይ መስዋእትነትን ያደረገ አንጋፋ ታጋይ የውስጥ አርበኛ ተባለ? እኚህ ጉግ ማንጉግ እኮ አያፍሩም! አሁን ከጠቅላላ የጽሑፎቹ ይዘትና ቃና የተረዳሁት ነገር ቢኖር ሁለቱ ጸሓፊዎች በኢሕአፓ አመራር የነበሩ ሰዎች ናቸው፣ ዘርኡ ክሕሽንን መዝለፋቸው የሚያስደንቀኝ አይሆንም። የጓዶቻቸው ስም ማጥፋትና ማንኳሰስ የጀመሩት ገና ፓርቲው ጨቅላ በነበረ ሰዓት ነው፣ ብርሃነመስቀል ረዳና ጌታቸው ማሩን 'ሀ ና ለ' ይሏቸው ነበር፣ አቶ ዘርኡ ክሕሽን ወደ ሱዳን በዘለቁ ግዜም 'ጓድ ኤክስ' (comrade x) የሚል ስያሜ ሰጧቸው። አቶ ብርሃነመስቀል ረዳ በደርግ ከተረሸኑ በኋላም ከማዘንና ለትግሉ ያደረጉትን አስተዋጽኦ ከመግለጽ ፋንታ Death of a Renegade (የከሃዲ ሞት) በሚል ርእስ ጽሑፍ አሰራጩ። ስለሆነም እነ አውግቸው ከዳተኛ ብሎ መሳደብ የቆየ ልምዳቸው ነውና የኔና የሌሎች ሰዎች ስም ከከሃዲዎች ጋር ማስቀመጣቸው የሚያስገርም አይሆንም። ግን በስድብ ባህል ብቻ የተወሰኑም አልነበሩም፣ ጓዶቻቸውን (ተቃዋሚ ወይም ሰላይ ተብሎ የተጠረጠሩትን) በአሲምባ የሚስጢር እስር ቤት ውስጥ የስቃይ ቅጣት እንዲደርስባቸው ከማድረጋቸውም በላይ የረሸኗቸውም አሉ፣ እነ ይርጋ ተሰማ (መዝሙር)፡ ና ታሪኩ/ኤልያስ ሌሎችም ታጋዮች ሠራዊቱ ባላወቀው መንገድ ተገድሏል። አቶ ጸሎቴ ህዝቅያስም በአንድ አስመሳይ ልክፍተኛ ወይም ዕብድ-መሳይ ታጋይ ቢገደልም የአሟሟቱ ሁኔታ ግን በጣም የሚያጠራጥር ነው። የኢሕአፓ የድሮ አመራር በብዙ ረገድ ይጠየቃል። ቀኑም ሲደርስ ወይም አቶ አውግቸው እንዳሉት የፍርድ ቀኑ ከፊታችን ሲደቀን ዳኛው ማን ይሆን የሚል ጥያቄ ማንሳት እንችላለን። በትንሳኤ ለፍርድ ግዜ ገዳዩ ዳኛ ከሆነ፣ ተገዳዩ ደግሞ ተከሳሽ ከሆነ ሙታኑ የነበሩበትን መቃብር ሊናፍቁት ነው። ነገር ግን በዘልማድ ዳኛ ወይም ዳኞች እንላለን እንጂ ለወደፊቱ ፈራጁ ምልአተ ሕዝቡ ነው የሚሆነው። በነዚህ በቅትለተ-ነብስ የተሳተፉ ሁሉ ህዝብ ይፋረዳቸዋል።

All Rights Reserved. Copyright © IDEA, Inc. July 30, 2008